# ትንቢተ ፡ ሐጌ ።

(ክለሳ.1.20020507)

## ትንቢተ ፡ ሐጌ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

### ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ በንጉሡ ፡ በዳርዮስ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በስድስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ እጅ ፡ ወደይሁዳ ፡ አለቃ ፡ ወደሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዘሩባቤል ፥ ወደ ፡ ታላቁም ፡ ካህን ፡ ወደኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

2 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፦ ዘመኑ ፡ አልደረሰም ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚሠራበት ፡ ዘመን ፡ አልደረሰም ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

3 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

4 ፤ በእውኑ ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ፈርሶ ፡ ሳለ ፡ እናንተ ፡ ራሳችኹ ፡ በተሸለሙ ፡ ቤቶቻችኹ ፡ ለመኖር ፡ ጊዜው ፡ ነውን ፧

5 ፤ አኹንም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ልባችኹን ፡ በመንገዳችኹ ፡ ላይ ፡ አድርጉ ።

6 ፤ ብዙ ፡ ዘራችኹ ፥ ጥቂትም ፡ አገባችኹ ፤ በላችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልጠገባችኹም ፤ ጠጣችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልረካችኹም ፤ ለበሳችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልሞቃችኹም ፤ ደመ ፡ ወዙን ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ በቀዳዳ ፡ ከረጢት ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ደመ ፡ ወዙን ፡ ተቀበለ ።

7 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ልባችኹን ፡ በመንገዳችኹ ፡ ላይ ፡ አድርጉ ።

8 ፤ ወደ ፡ ተራራው ፡ ውጡ ፥ ዕንጨትንም ፡ አምጡ ፥ ቤቱንም ፡ ሥሩ ፤ እኔም ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፥ እኔም ፡ እመሰገናለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

9 ፤ እናንተ ፡ ብዙ ፡ ነገርን ፡ ተስፋ ፡ አደረጋችኹ ፥ እነሆም ፥ ጥቂት ፡ ኾነ ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ ባገባችኹት ፡ ጊዜ ፡ እፍ ፡ አልኹበት ፦ ይህ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ እናንተ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እየቤታችኹ ፡ እየሮጣችኹ ፡ የእኔ ፡ ቤት ፡ ፈርሶ ፡ ስለ ፡ ተቀመጠ ፡ ነው ።

10 ፤ ስለዚህ ፥ ሰማያት ፡ በላያችኹ ፡ ጠልን ፡ ከልክለዋል ፥ ምድሪቱም ፡ ፍሬዋን ፡ ከልክላለች ።

11 ፤ እኔም ፡ በምድርና ፡ በተራራዎች ፥ በእኽልና ፡ በወይንም ፥ በዘይትና ፡ ምድርም ፡ በምታበቅለው ፡ ላይ ፥ በሰዎችና ፡ በእንስሳዎችም ፡ ላይ ፥ እጅም ፡ በሚደክምበት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ድርቅን ፡ ጠርቻለኹ ።

12 ፤ የሰላትያልም ፡ ልጅ ፡ ዘሩባቤል ፥ ታላቁም ፡ ካህን ፡ የኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ድምፅ ፡ የነቢዩንም ፡ የሐጌን ፡ ቃል ፥ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ላከው ፡ ኹሉ ፡ ሰሙ ፤ ሕዝቡም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ፈሩ ።

13 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልእክተኛ ፡ ሐጌ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልእክት ፡ ሕዝቡን ፦ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

14 ፤ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የይሁዳን ፡ አለቃ ፡ የሰላትያልን ፡ ልጅ ፡ የዘሩባቤልን ፡ መንፈስ ፥ የታላቁንም ፡ ካህን ፡ የኢዮሴዴቅን ፡ ልጅ ፡ የኢያሱን ፡ መንፈስ ፥ የቀሩትንም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ መንፈስ ፡ አስነሣ ፤ በንጉሡም ፡ በዳርዮስ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በስድስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ መጡ ፥ የአምላካቸውንም ፡ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሠሩ ።

## ትንቢተ ፡ ሐጌ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

### ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያ ፡ አንደኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሲል ፡ መጣ ፦

2 ፤ ለይሁዳ ፡ አለቃ ፡ ለሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ለዘሩባቤል ፥ ለታላቁም ፡ ካህን ፡ ለኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ለኢያሱ ፥ ለቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ተናገር ።

3 ፤ በቀድሞ ፡ ክብሩ ፡ ሳለ ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ያየ ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ የቀረ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ዛሬስ ፡ እንዴት ፡ ኾኖ ፡ አያችኹት ፧ በዐይናችኹ ፡ እንደ ፡ ምናምን ፡ አይደለምን ፧

4 ፤ አኹን ፡ ግን ፥ ዘሩባቤል ፡ ሆይ ፥ በርታ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ታላቁም ፡ ካህን ፡ የኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ሆይ ፥ በርታ ፥ እናንተም ፡ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ በርቱና ፡ ሥሩ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

5 ፤ መንፈሴም ፡ በመካከላችኹ ፡ ይኖራልና ፥ አትፍሩ ።

6 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ገና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቅርብ ፡ ዘመን ፡ እኔ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ ባሕርንና ፡ የብስንም ፡ አናውጣለኹ ፤

7 ፤ አሕዛብን ፡ ዅሉ ፡ አናውጣለኹ ፥ በአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ የተመረጠውም ፡ ዕቃ ፡ ይመጣል ፤ ይህንም ፡ ቤት ፡ በክብር ፡ እሞላዋለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

8 ፤ ብሩ ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ ወርቁም ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

9 ፤ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ የዚህ ፡ የኋለኛው ፡ ቤት ፡ ክብር ፡ ይበልጣል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ሰላምን ፡ እሰጣለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

10 ፤ በዳርዮስም ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

11 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ካህናቱን ፡ ስለ ፡ ሕጉ ፡ ጠይቅ ፤

12 ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ የተቀደሰ ፡ ሥጋ ፡ በልብሱ ፡ ዘርፍ ፡ ቢይዝ ፥ በዘርፋም ፡ እንጀራ ፡ ወይም ፡ ወጥ ፥ ወይም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ ወይም ፡ ዘይት ፥ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ መብል ፡ ቢነካ ፡ ያ ፡ የተነካው ፡ በእውኑ ፡ ይቀደሳልን ፧ ብለኽ ፡ ካህናቱን ፡ ጠይቃቸው ፤ ካህናቱም ፦ አይኾንም ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

13 ፤ ሐጌም ፦ በሬሳ ፡ የረከሰ ፡ ሰው ፡ ከነዚህ ፡ አንዱን ፡ ቢነካ ፡ ያ ፡ የተነካው ፡ በእውኑ ፡ ይረክሳልን ፧ አለ ። ካህናቱም ፦ አዎን ፡ ይረክሳል ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

14 ፤ ሐጌም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ይህ ፡ ሕዝብና ፡ ይህ ፡ ወገን ፡ በፊቴ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የእጃቸውም ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤ በዚያም ፡ ያቀረቡት ፡ ነገር ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

15 ፤ አኹንም ፡ ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ሳይነባበር ፥ ከዛሬ ፡ ዠምራችኹ ፡ ወዳለፈው ፡ ዘመን ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።

16 ፤ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ዅሉ ፡ ሰው ፡ ኻያ ፡ መስፈሪያ ፡ ወዳለበት ፡ ምርት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ የተገኘው ፡ ዐሥር ፡ መስፈሪያ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ዐምሳ ፡ ማድጋም ፡ ይቀዳ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መጥመቂያው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ የተገኘው ፡ ኻያ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

17 ፤ በእጃችኹ ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ በዋግና ፡ በዐረማሞ ፡ በበረዶም ፡ መታኋችኹ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሳችኹም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

18 ፤ ከዛሬው ፡ ከዘጠነኛው ፡ ወር ፡ ከኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ዠምራችኹ ፡ የሚመጣውን ፡ ዘመን ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ መሠረት ፡ ከተተከለበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።

19 ፤ ዘር ፡ በጐተራ ፡ ገና ፡ ይኖራልን ፧ ወይንና ፡ በለስ ፡ ሮማንና ፡ ወይራ ፡ አላፈሩም ፤ ከዚች ፡ ቀን ፡ ዠምሬ ፡ እባርካችኋለኹ ።

20 ፤ በወሩ ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኹለተኛ ፡ ወደ ፡ ሐጌ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦



www.ethiopianorthodox.org

21 ፤ ለይሁዳ ፡ አለቃ ፡ ለዘሩባቤል ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በል ፦ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ አናውጣለኹ ፤

22 ፤ የመንግሥታትንም ፡ ዙፋን ፡ እገለብጣለኹ ፥ የአሕዛብንም ፡ መንግሥታት ፡ ኀይል ፡ አጠፋለኹ ፤ ሠረገላዎችንና ፡
የሚቀመጡባቸውንም ፡ እገለብጣለኹ ፤ ፈረሶችና ፡ ፈረሰኛዎቻቸውም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በወንድማቸው ፡ ሰይፍ ፡
ይወድቃሉ ።

23 ፤ ባሪያዬ ፡ የሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ዘሩባቤል ፡ ሆይ ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ እወስድኻለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ፤ እኔ ፡ መርጬኻለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እንደ ፡ ቀለበት ፡ ማተሚያ ፡ አደርግኻለኹ ፥ ይላል ፡
የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፨



www.ethiopianorthodox.org